

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኖቬምበር 11-20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

# እንዲሁም ከኖቬምበር 21-30፣ ከዲስምበር 1-10/2025

# የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2025

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ የተሻለ ገጽታ ነበራቸዉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የተሻላ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ አና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ10 ሚ.ሜ በላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ጎንደር 27.3፣ 15፣ 16.5፣ ጎሬ 13.3፣ 13.7፣ አዴት 36፣ አደዋ 16.2፣ አይራ 18.3፣ 12.8፣ አማን 10.8፣ አይከል 24.9፣ በደሌ 13፣ ቡሬ 31.5፣ 28፣ ደምቢ ዶሎ 11.5፣ 17.2፣ ፉኙዶ 12.8፣ 25፣ ጊዳ አያና 39.2፣ ላሬ 21፣ ላይብር 10.2. ሞጣ 12.4፣ ሳዉላ 22፣ 15፣ ሽሬ 22.7፣ አቦ ሞሪንጋ 33.6፣ 12.8፣ አሺ 14፣ 10.4፣ ቡልቂ 25.9፣ ዳባት 14.32፣ ፉጉ ሌቃ 14.5፣ 13.5፣ 16.2፣ ጌጫ 18፣ 26፣ 16፣ 19፣ ቅዳሜ ገበያ 27.8፣ 36.8፣ 16.9፣ 28.8፣ 16.7፣ ኮበን 23፣ 11፣ ኪሚ 13.5፣ ሙጊ 11.4፣ 47.5፣ 14.7፣ 29.4፣ ኦንጋ 14.3፣ ሮብ ገበያ 17.8፣ ሲቦ 11.4፣ ትንሹ መጢ 18.3፣ መንደር አስራ ሶስት 16፣ እንዲሁም ያንፋ 22.2.፣ 28.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በአስራ ስድስት (16) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ የሆነ መካከለኛ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡

Ethiopian Meteorology Institute





ምስል፡1 ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው


ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ጥቂት የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ጥቂት የዳዋ ዞኖች ላይ ከ6-20 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ1 እና 2)፡፡ በተመሳሳይ ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ እያገኙ የነበሩት ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ31-111 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ ሰሜን ምዕራብ እና የምዕራብ ትግራይ ዞኖች፤ በሰሜን፣ በመካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር፣ በህር ዳር ዙሪያ፣ በሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፤ የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ካማሺ፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ መተከል ዞኖች፣ በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ከ6-40 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እሰከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከ2-8 ቀናት ያህል ተመዝግቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር


በሌላ በኩል ባለፉት አስር ቀናት የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች ተመዝግቧል (ምስል 2)፡፡




ምስል 2፡ ከኖቬምበር 11-20 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ በሌላም በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምራብ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ ዕድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች ጠቀሜታ ነበረው። በአንጻሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች  በተለይም በተወሰኑ በደቡብ ክልል ደቡባዊ ዞኖች፣ በቦረናና ጉጂ ዞኖች ላይ የነበረው እርጥበት ቀደም ሲል ለተዘሩ ሰብሎች ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ሲሆን ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻልና የዝናብ ውሃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት ገንቢ ሚና ነበረው። በሌላም በኩል አልፎ አልፎ በተለይም በሰሜን፣ በሰሜን ምራብና በመእራብ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በመጠኑም ቢሆን አሉተዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ መረብ ጋሽ፣ በመካከለኛው እና ታችኛው አባይ፣ ተከዜ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በጥቂት ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ እንዲሁም በጥቂት ታችኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች የተሻለ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እና የተፋሰሶችን የስነ-ምህዳር ደህንነት ከማረጋገጥ አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በአንጻሩ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ተከዜ እና አይሻ ተፋሰሶች በአብዛኛው ደረቅ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ቆይተዋል (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝንበት ሳምንት ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ፣ መካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ይዘወተራል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ውርጭ የማስከተል ጥንካሬ ይኖረዋል። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡


## 2.1 እ.ኤ.አ ከኖቬበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር የሶስተኛዉ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በጥቂት የቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡ በመሆኑም የሚኖረው አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ በአግባቡ በመሰብሰብ ሊኖር የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መቀነስ ያስፈልጋል (ካርታ 6)፡፡

በሌላ በኩል ከሚኖረው የደመና ሽፋን ላይ በመነሳት በጥቂት የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤ የምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፤ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ የጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡ ስለሆነም በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች የደረሱ ሰብሎች መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይጠቁማል፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 21-30, 2025
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 21-30, 2025
የሚኖረዉ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| አሮሚያ | ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ዳዋ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

| በጥቂት አከባበቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፤ የምዕራብ የሸዋ እና የደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ፣ ጥቂት የደቡብ ወሎ፣ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | በጥቂት የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የምስራቅ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | በጥቂት ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ሰሜን እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ምስል 2)።




ምስል፡2 ከኖቬምበር 21-30 በ24 ሰዓት ውስጥ ከሁለት (2) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የሚመዘገብባቸው ስፍራዎች

Ethiopian Meteorology Institute

## 2.2 እ.ኤ.አ ከዲሲምበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የዲሴምብር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በሌላ በኩል በመካከለኛዉ፣ ምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ።

## 2.3 እ.አ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብ እና ደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አርብቶ አደሮች እና ከፊል የአርብቶ አደር ዞኖች ላይ የሚኖረው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በሌላም በኩል መኸር አብቃይ በሆኑት ክልል ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረ ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ዞኖች ዳዋ፣ ሊበን እና አፍዴር ዞኖች ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ቦሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• በደጋማ አካባቢዎች ለተዘሩ ሰብሎች እድገት<br>• ለአርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን<br>• ከፍተኛ ትነት | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የእንስሳት መኖ ከሰብል ተረፈ ምርት ማሰባሰብ እና ማከማቸት<br>• ደጋማ አካባቢዎች ሰብሎች በአረም እንይጎዱ የማስወገድ ስራዎችን ማከናወን |
| **የመኸር ሰብል አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ባሌ፣ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት ለተዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች እድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ልምላሜ<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት<br>• የውርጭ ስጋት መቀነስ | • ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የደረሱ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል<br>• ከእርጥበትና ሙቀት ጋር ተያይዞ የዋግ በሽታ ስጋት መኖር | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ቀናቶች መሰብሰብ<br>• የጥራጥሬ ሰብሎች (ሽንብራ እና ጓያ) እድገትን መከታተል<br>• በደጋና በውይን አደጋ አካባቢ የሰብል በሽታ ክትትል ማድረግ |
| **ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የሚጠበቅባቸው ዞኖች** | | | | |
| አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ የሸዋ እና የደቡብ ምዕራብ የሸዋ ዞኖች፣ ጥቂት የደቡብ ወሎ፣ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች በጥቂት የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና በጥቂት | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት | • በመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ አነስተኛ | • የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት የመሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ማከናወን |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ የምስራቅ ትግራይ ዞኖች | | | አሉታዊ ተጽዕኖ<br>• በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ የለሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ መጨመረ | አልፎ አልፎ የውርጭ ክስተት በሚጠበቅባቸው አንዳንድ አካባቢዎች በሰብሎችና በመስኖ በሚበቅሉ አዝዕርቶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሶስተኛ አሥር ቀናት በጥቂት ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ የሚጠበቀው እርጥበት የገፀ ምድር የውሃ ፍሰትን በመጠኑ እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ሲሆን የተቀሩት በአብዛኛው ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘረፉ አካላት የቀረቡትን የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም አሉታዊ ተፅኖዎች መቀነስ አስገላጊ ነው።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በላይኛ ባሮ አኮቦ፣ በላይኛ እና በመካከለኛው አሞጊቤ፣ በጥቂት መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ እንዲሁም በላይኛው ገናሌ ዳዋ | መካከለኛ የእርጥበት መጠን | • ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም ለመጠጥ ውሃ መጠነኛ የውሀ አቅርቦት መኖር | • አንጻራዊ የትነት መጨመርና የግድቦች ውሃ መቀነስ | • ከብክነት እንዲሁም ከብለት መጠበቅ ውሃን በተገቢ ሁኔታ ማሰባሰብ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አባይ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | | • የወንዞች እንዲሁም በሌሎች የዉሃ አካላት መጠን መቀነስ በመጠጥ ዉሃ እና ሌሎች ዉሃ አገልግሎት ተፅኖ መፍጥር | • የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል ማሰባሰብ |

Ethiopian Meteorology Institute